# የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነት እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ የሚያገለግልበት ሁኔታ ከኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንፃር ሲገመገም (Assessment of Prior Criminal Conviction as A General Penalty Aggravating Factor Under the Criminal Code of Ethiopia)

**ዶ/ር ደጀኔ ግርማ ጃንካ***

## ረቂቅ ፅሁፍ (Abstract)

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሠላም፣ ደህንነት እና መረጋጋት እንዲኖር ለማድረግ ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ የሕግ ማዕቀፎች መካከል አንዱ የወንጀል ሕግ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ ሰዎች መፈፀም የማይገባቸውን ድርጊቶች እና ማከናወን የሚገባቸውን ተግባራት በዝርዝር የሚደነግግ ሲሆን ድንጋጌው ሳይከበር ሲቀር ጥፋተኞቹ እንዲቀጡ ያዝዛል፡፡ በተፈፀሙ ወንጀሎች ምክንያት በጥፋተኞች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች በተጣሱ ድንጋጌዎች መሰረት የሚለዩ ሲሆን እንደ ሁኔታው እነዚህ ቅጣቶች ሊቀሉ ወይም ሊከብዱ ይችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሰረት ቅጣት እንዲከብድ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ ነው፡፡ ነገር ግን የቀደመ የወንጀል ሪከርድ መኖሩ በቀጥታ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ቅጣት እንዲከብድ የሚያደርግ ሁኔታ ሳይሆን አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ቅጣት የማክበድ ውጤት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የተቃኘው ጉዳይም ከሀገራችን የወንጀል ሕግ አንፃር የአንድ ሰው የቀደመ የጥፋተኛነት ታሪክ/ሪከርድ እንደ ጠቅላላ የቅጣት መክበጃ የሚያገለግለው መቼ ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ የህትመት ስራዎች ዳሰሳ በማድረግ የወንጀል ሪከርድ ትርጉም እና ውጤቱ ምን እንደሆነ ታይቷል፤ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ ተቃኝቷል፤ ተገቢነት ያላቸው የሀገራችን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተተንትኗል፤ በጉዳዩ ላይ የሕግ ባለሙያዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሳኔንም ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ በዚሁ አግባብ ፅሁፉ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ/ታሪክ እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ሊያገለግል የሚችለው ጥፋተኛው ቀድሞ በተጣለበት ቅጣት መሰረት የመማር እድል አግኝቶ በዚህ ዕድል በመጠቀም ሳይማር ከቀረ እና ሌላ ወንጀል ፈፅሞ ከተገኘ ብቻ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ነገር ግን ከቀድሞ ጥፋቱ እና ቅጣቱ ያልተማረውንም ሰው ቢሆን የቀደመ የወንጀል ሪከርድ እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ የመጠቀሙ ሁኔታ ገደብ የለሽ እንዳልሆነ ፅሁፉ አሳይቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት (Key words) ፡** ወንጀል፣ ጥፋተኛነት፣ ቅጣት፣ የወንጀል ሪከርድ፣ የቅጣት ማክበጃ፣ የቅጣት ማቅለያ

---

* ፀሃፊው (LLB, LLM, PHD) የሕግ መምህር፣ ተመራማሪ፣ አማካሪ እና ጠበቃ ናቸው፡፡ የዚህን ፅሁፍ ረቂቅ በማንበብ ፅሁፉ እንዲዳብር አስተያየት የሰጡኝ ባልደረቦቼ ዶ/ር አለሙ ምህረቱ እና ዕጩ ዶ/ር ጎሳዬ አየለ በጣም አመሰግናቸዋለሁ፡፡ እንዲሁም ማንነታቸውን የማላውቃቸው ገምጋሚዎች ለሰጣችሁኝ ገንቢ አስተያየት አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ በተረፈ በፅሁፉ ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች የፀሃፊው ናቸው፡፡ ፀሃፊውን በ dejulaw@gmail.com ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

## 1. *መግቢያ*

በአንድ ሀገር ውስጥ መሰረታዊ ከሆኑ ህጎች መካከል አንዱ የወንጀል ሕግ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጋራ ጥቅም ሲባል የአንድን ሀገር መንግስት፣ ህዝቦች እና ነዋሪዎች ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርዓት፣ መብቶች እና ጥቅም እንዲከበር ማድረግና ማረጋገጥ ነው፡፡[1] ይህን ለማድረግ የወንጀል ሕግ ሁለት ዘዴዎች ይጠቀማል፡፡[2] አንደኛው አስቀድሞ ወንጀል ስለሆኑ ድርጊቶች እና ተፈፅሞ ሲገኙ ስለሚያስከትሏቸው ውጤቶች ለህብረተሰቡ ማሳወቅና የወንጀል ድርጊቶቹ እንዳይፈፀሙ ማስጠንቀቂያ መስጠት ነው፡፡ ሁለተኛው በህጉ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ውጤት ያላስገኘ እንደሆነ ቅጣት እና የእርምት እርምጃዎችን መጠቀም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የወንጀል ሕግ ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለውን የቅጣት ወሰን የሚያስቀምጥ ሲሆን በወንጀል ድርጊት ተከሳሽ የሆነ ሰው ጥፋተኛነቱ ከተረጋገጠ ይህ ቅጣት ተግባራዊ ይደረግበታል፡፡[3] በሌላ በኩል የወንጀል ህጉ በልዩ ክፍሉ የደነገጋቸው ቅጣቶች መቅለል ወይም መክበድ እንዲችሉ የሚያደርጉ በርካታ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህ የቅጣት ማቅለያዎችና ማክበጃዎች *ጠቅላላ* እና ልዩ በመባል በህጉ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡[4] የወንጀል ህጉ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች የሚላቸውን ሁኔታዎች በዋናነት በአንቀፅ 84 ስር የደነገጋቸው ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱ የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነት ታሪክ ወይም በተለምዶ የወንጀል ሪከርድ የሚባለው ነው፡፡[5]

አንድ ሰው የወንጀል ክስ ቀርቦበት በዚህ ክስ መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ዐ/ሕግ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1(ሐ)) መሰረት ጥፋተኛው ቀድሞ በሌላ ወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ ስለሆነ (የወንጀል ሪከርድ ስላለበት) ይህ ሁኔታ እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ እንዲያዝለት ለፍ/ቤት ያመለክታል፤ በተከሳሽ በኩል የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ያለ መሆኑ ከታወቀ በቀረበው የቅጣት ማክበጃ አስተየየት ላይ እምብዛም ተቃውሞ አይነሳም፤ ፍ/ቤትም የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነት መኖሩ ከታመነ ወይም ከተረጋገጠ ያለ ተጨማሪ ምርመራ ቅጣት ያከብዳል፡፡[6] ይህ አሰራር ያለ እና ለወደፊት ለመቀጠልም ሰፊ እድል አለው፡፡

ነገር ግን የወንጀል ህጋችን የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነት በአንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ቅጣትን ለማክበድ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈቅደው መቼ ነው? ይህ ጥያቄ ተገቢ ማብራሪያ እና መልስ ማግኘት ያለበት ነው፡፡ በጥያቄው ላይ የባለሙያዎች ሀሳብና አቋም ወጥ አይደለም፡፡ አንድ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ከሚያስፈልገው በታችም ወይም በላይ መቅጣት ትክክል ስለማይሆን[7] በወንጀል ሕጉ የተደነገጉ የቅጣት ማክበጃዎች ህጉ በሚያስባቸው ጊዜ እና ሁኔታ ብቻ ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

---

[1]የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንልጅ ህግ፣ 1996 ዓ.ም.፣ አንቀፅ 1 ይመልከቱ፡፡

[2] ስለዚህ ነጥብ በስፋት ለመገንዘብ Dejene Girma Janka, A Handbook on the Criminal Code of Ethiopia (Revised Edition, Far East Trading P.L.C, 2021) 7-10 ይመልከቱ፡፡

[3] በተለየ ሁኔታ የተወሰነው ቅጣት ሳይፈፀም ተገድቦ እንዲቆይ ስለሚፈቅድ ፍ/ቤቶች አፈፃፀምን ሊገድቡ ይችላሉ፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንልጅ ህግ፣ 1996 ዓ.ም.፣ አንቀፅ 190 እና 192ን ይመልከቱ፡፡

[4] ለማቅላያዎች የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 82 እ 83 እንዲሁም ለማክበጃዎች አንቀፅ 84 እና 85 ይመልከቱ፡፡

[5] የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 84(1(ሐ)) ይመልከቱ፡፡

[6] የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ የጥብቅና ስራ የሚሰሩ በመሆናቸው እንደዚህ ዓይነቱን ተግባር በየጊዜው የሚመለከቱት ክስተት ነው፡፡ በተጨማሪ በሌላ ክፍል ውስጥ ለዚህ መረጃ ደጋፊ የሚሆን የፍ/ቤት ጉዳይ የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

[7] በእኛ ሀገር ሁኔታ የወንጀል ህግ ዓላማ ብቀላ ስላልሆነ የቅጣት ትክክለኛነት መታየት የሚገባው ከቅጣት አላማ አንፃር ነው እንጂ ከደረሰው ጉዳት አንፃር አይደለም፡፡

ይህ ፅሁፍ ከላይ የተነሳውን ጥያቄ የሕግ ትንተና በማድረግ ለመመለስ ይሞክራል፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ፅሁፉ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል ከላይ የቀረበውን የመግቢያ ሀሳብ የያዘ ነው፡፡ በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ስለ ቅጣት እና ቅጣት ማክበጃ አጠር ያለ ሀሳብ ቀርቦበታል፡፡ ሶስተኛው ክፍል የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነት ምንነት እና ቅጣትን ማክበድ ያለበት መቼ እንደሆነ ከወንጀል ህጉ መንፈስ አንፃር ትንታኔ የተደረገበት ነው፤ እንዲሁም በዚህ ክፍል ውስጥ በጉዳዩ ላይ የባለሙዎች ሀሳብ/አቋም ምን እንደሆነ ለማወቅ የፖል ጥያቄ ተጋጅቶ 211 የሕግ ባለሙያዎች ድምፅ እንዲሰጡበት (183 የሕግ ባለሙያዎች በቴሌግራም እና ከ28 የሕግ ባለሙያዎች በፌስቡክ) ተደርጎ የተገኘውን ሀሳብ አጠር ባለ ሁኔታ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች በእለት ተዕለት ስራቸው ውስጥ ከጉዳዩ ጋር የሚገናኝ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ በጥናቱ ውስጥ የእነርሱን ሀሳብ/አቋም ማካተት ወሳኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የፅሁፉ የመጨረሻ ክፍል መደምደሚያ ሃሳብ የቀረበበት ነው፡፡

## 2. ቅጣት እና የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች

ቶማስ ሆብስ (Thomas Hobbes) የሚባል ፈላስፋ ቅጣት ማለት *ሰዎች ለሕግ ተገዥ እንዲሆኑ ለማድረግ ሕግን በመጣስ አታድርግ የተባለውን ነገር ባደረገ ሰው ወይም አድርግ የተባለውን ነገር ሳያደርግ በቀረ ሰው ላይ ስልጣን ባለው አካል እንዲደርስ የሚደረግ ጉዳት ነው* በማለት ትርጉም ይሰጣል፡፡[8] ሃርበርት ሊዮኔል አዶልፈስ ሃርት (H.L.A. Hart) የሚባል ሌላው ምሁር ቅጣት ማለት *ሕግ በመጣሱ ምክንያት በጥፋተኞች ላይ ስልጣን ባለው አካል እንዲደርስ የሚደረግ ጉዳት ወይም የማይመች (unpleasant) ውጤት የሚያስከትል እርምጃ ነው* በማለት ለቃሉ ትርጉም ይሰጣል፡፡[9] እነዚህ ሁለቱ ምሁራን ቅጣት ለሚለው ቃል ከሰጡት ትርጉም ውስጥ በርከታ ነገሮችን መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ቅጣት የሚጣለው የሕግ ጥሰት (ወንጀል) ሲኖር ብቻ እንደሆነ፤ ቅጣት የሚጣለው ስልጣን ባለው አካል (በመንግስት) ብቻ እንደሆነ፣ መቅጣት ማለት ጥፋተኛ በሆነ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም የማያስደስት ስሜት ሊፈጥር የሚችል እርምጃ መውሰድ እንደሆነ ከትርጉሞቹ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቅጣት ሰዎች እንዳያጋጥማቸው የሚፈልጉት እና በተቻለ መጠን ሊያስወግዱት የሚመኙት ሁኔታ ወይም እርምጃ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሀገራችን ቅጣት የሚለው ቃል በወንጀል ህጉ መሰረት ትርጉም የተሰጠው ቃል አይደለም፡፡ ሆኖም ግን የወንጀል ህጉ የተለያዩ ወንጀሎች ተፈፅሞ ሲገኙ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል የቅጣት መጠን ምን ያክል እንደሆነ እና ይህ ቅጣት መቼ እና በምን አግባብ ሊከብድ ወይም ሊቀል እንደሚችል ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ ለምሳሌ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ናቸው ተብለው የታሰቡ ሁኔታዎች በዋናነት በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84 ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡[10] የቅጣት ማክበጃ ሁኔታ ለተፈፀመው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት እንዲጨምር የሚያደርግ ምክንያት ሲሆን ቅጣቱ እንዲቀንስ የሚያደርግ ምክንያት ደግሞ የቅጣት ማቅለያ

[8] Thomas Hobbes, Leviathan, (Oxford University Press, New York, 1996) 205.
[9] H.L.A Hart, Punishment and Responsibility: Essays in the Philosophy of Law (2nd ed, Oxford University Press, New York, 1968) 4-5.
[10] ተጨማሪ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎችን ፍ/ቤቶች በወንጀል ህግ አንቀፅ 86 መሰረት ሊቀበሉ ይችላሉ፡፡

በመባል ይታወቃል፡፡[11] ስለዚህ ወንጀል ተፈፅሞ ከተገኘ በወንጀለኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት አስፈላጊ የሆኑ ምክንያቶች እስከተሟሉ ድረስ ማቅለልም ሆነ ማክበድ ይቻላል፤ ይህም በተለያዩ ሀገሮች የተለመደ አሰራር ነው፡፡

ለምሳሌ በአሜሪካ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ፀፀት አለማሳየት ወይም በህፃን ፊት ወንጀል መፈፀም ቅጣትን ከሚያከብዱ ሁኔታዎች መካከል ናቸው፡፡[12] በጀርመን የግድያ ወንጀልን ደስታ ለማግኘት፣ በስግብግብነት፣ ወይም ሌላ ወንጀል ለመደበቅ የተፈፀመ ከሆነ እነዚህ ሁኔታዎች ቅጣት የሚያከብዱ ናቸው፡፡[13] በደቡብ አፍሪካ በዋስትና ላይ እያሉ ወንጀል መፈፀም፣ በቡድን ሆኖ ወንጀል መፈፀም፣ ወንጀልን ሙያ አድርጎ መፈፀም፣ የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ወንጀልን መፈፀም፣ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ማስረጃ ለማጥፋት መሞከር፣ በተወሰኑ ቡድኖች ላይ በሚኖር ጥላቻ ምክንያት ወንጀል መፈፀም፣ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ሆን ብሎ ለይቶ እነርሱ ላይ ወንጀል መፈፀም፣ ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ወንጀል መፈፀም፣ ወዘተ ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ናቸው፡፡[14] በህንድ በልጆች እና ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍል ላይ ወንጀል መፈፀም እና የጥላቻ ወንጀሎችን መፈፀም ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ናቸው፡፡[15]

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደሚያሳዩት ቅጣት በብዙ ምክንያት ሊከብድ የሚችል እርምጃ ሲሆን ቅጣት የማክበዱ ሁኔታዎችም በተለያዩ ሀገሮች ተግባራዊ እየተደረገ ያለ አሰራር ነው፡፡ ከእነዚህ ቅጣት ከሚያከብዱ ሁኔታዎች መካከል የቀደመ የወንጀል ታሪክ (ሪከርድ) ይካተትበታል ወይ የሚለው ነጥብ የዚህ ፅሁፍ ምሰሶ በመሆኑ *በምንነቱ* እና በ*ውጤቶቹ* ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ቀርቧል፡፡

## 3. የቀደመ የወንጀል ጥፋተኝነት (ሪከርድ) እንደ ቅጣት ማክበጃ

### 3.1. ትርጉም

በካምብሪጅ መዝገበ-ቃል መሰረት የወንጀል ሪከርድ ማለት *አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሞ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ኦፊሴላዊ ሪከርድ ነው* ማለት ይቻላል፡፡[16] ሰፋ ተደርጎ ሲታይ ደግሞ የወንጀል ሪከርድ/ታሪክ ማለት *አንድ ሰው ከወንጀል ፍትህ ስርዓት ጋር ያለው*

---

[11] How Sentences are imposed, Government of Canada, ‹https://www.justice.gc.ca/eng/cj-jp/victims-victimes/sentencing-peine/imposed-imposees.html› accessed on 28 November 2023.
[12] በዚህ ነጥብ ላይ የበለጠ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ ይህን ምንጭ ይልከቱ፡ Aggravating Factor, ‹available at https://www.law.cornell.edu/wex/aggravating_factor#:~:text=Typical%20examples%20of%20aggravating%20factors,Procedure%2C%20and%20the%20Death%20Penalty› accessed on 19 November 2023.
[13] በዚህ ነጥብ ላይ ለበለጠ መረጃ የጀርመን የወንጀል ህግ፤ እ.አ.አ. በ1998፣ ክፍል 211 ይመልከቱ፡፡
[14] በዚህ ነጥብ ላይ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ እ.አ.አ. ከ 01 October 2019 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነ በ "Sentencing Guidelines Council" የተዘጋጀ የደቡብ አፍሪካ General guideline: overarching principles, ‹https://www.sentencingcouncil.org.uk/overarching-guides/crown-court/item/general-guideline-overarching-principles/› accessed on 19 November 2023 ይመልከቱ፡፡
[15] በዚህ ነጥብ ላይ የበለጠ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ ይህን ምንጭ ይመልከቱ፤ Yash Jain, Aggravating Factor in Sentencing Policy ‹https://www.legalserviceindia.com/legal/article-3063-aggravating-factor-in-sentencing-policy.html› accessed on 19 November 2023.
[16] Cambridge Dictionary, Criminal Record ‹https://dictionary.cambridge.org/dictionary/english/criminal-record› accessed on 19 November 2023.

መስተጋብር *ወይም ግንኙነት ሲሆን ይህም በወንጀል ምክንያት ቀድሞ መያዝን፣ ማረፊያ ቤት መቆየትን፣ ጥፋተኛ መባልን፣ ወዘተ ያጠቃልላል* ሊባል ይችላል፡፡[17] እንዲሁም የወንጀል ሪከርድ ማለት *ከወንጀል ጋር የተያያዘ ኦፊሴላዊ ሪከርድ ሆኖ ስለ አንድ ሰው በወንጀል ምክንያት የመያዝ፣ የመከሰስ፣ እና የመቀጣት ታሪክ ማለት ነው* ሊባል ይችላል፡፡[18] ከእነዚህ ትርጉሞች የወንጀል ሪከርድ (ታሪክ) ኦፊሴላዊ መረጃ መሆኑን እና ከወንጀል ሕግ ወይም ከወንጀል ፍትህ ስርዓት ጋር መስተጋብር ሲፈጥር የሚኖር ሁኔታ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የወንጀል ሪከርድ/ታሪክ ስለ አንድ ሰው በወንጀል ተጠርጥሮ መያዝ፣ ማረፊያ ቤት መቆየት፣ መከሰስ፣ ወይም ጥፋተኛ መባል የሚያመለክት መረጃ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሀገራችን ሕግ መሰረት የቀደመ የወንጀል ታሪክ ወይም ሪከርድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልፅ የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተጠቀሱት ትርጉሞች በተለየ መልክ በፍርድ ቤቶቻችን ዘንድ ቅጣት ለመወሰን ዓላማ *የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ* የሚለው ሀሳብ በወንጀል ተጠርጥሮ መያዝን፣ ማረፊያ ቤት መቆየትን፣ እና መከሰስን አይጨምርም፡፡ በወንጀል ሕጉ መሰረት ከቅጣት ማክበድ ጋር እንዲገናኝ የተፈለገው ሁኔታ አንድ ሰው በአጠቃላይ ከወንጀል ፍትህ ስርዓት ጋር የነበረው መስተጋብር ሳይሆን በወንጀል ከተከሰሰ በኋላ የጥፋተኛነት ውሳኔ የተላለፈበት መሆኑን የሚገልፅ ታሪክ ወይም ሪከርድ ወይም መረጃ ብቻ እንደሆነ ከሕጉ አንቀፅ 67 እና 84(1)(ሐ) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው በወንጀል ተጠርጥሮ ተይዞ ወይም ክስ ተመስርቶበት የነበረ መሆኑን የሚገልፅ መረጃ ቢኖርም መረጃው በፍርድ ቤቶች ዘንድ ቅጣት ለማክበድ እንደ ወንጀል ሪከርድ የሚታይ አይደለም፡፡

### 3.2. የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ ውጤት

የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ ምንነት ከተገለፀ በኋላ *የዚህ ሪከርድ መኖር በኋላ (በድጋሚ) ከሚፈፀመው ወንጀል አንፃር ውጤቱ ምንድን ነው?* የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥያቄ ከመመለሱ በፊት በፍ/ቤቶች ዘንድ ከግምት ውስጥ የሚገባው የወንጀል የጥፋተኛነት ታሪክ በሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች የተሰጡት ብቻ ናቸው ወይስ በሌሎች ሀገሮች ፍ/ቤቶች የተሰጡትንም ይጨምራል? የሚለውን ነጥብ በአጭሩ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

አንዳንድ ሀገሮች አልፎ አልፎ በሌላ ሀገር የተሰጠ የወንጀል ሪከርድ በሀገራቸው የወንጀል የባህር መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ በጀርመን በሌሎች ሀገሮች የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች በማዕከላዊ የወንጀል መዝገብ (Central Criminal Register) ላይ የሚመዘገቡበት ሁኔታ ሲኖር ምዝገባው ተከናውኖ ሲገኝ የውጪ ፍ/ቤት የጥፋተኛነት ውሳኔ እንደ ሪከርድ ለቅጣት ማክበድ ሊያገለግል ይችላል፡፡[19]

---

[17] ለበለጠ *መረጃ* Criminal Record Online Toolkit, ‹ https://cjei.cornell.edu/about-your-record/what-criminal-record-or-criminal-history› accessed on 19 November 2023 *ይመልከቱ፡፡*
[18] James F. Nelson, An Operational Definition of Prior Criminal Record (1989) 5 Journal of Quantitative Criminology 4, 334.
[19] The Federal Central Criminal Register, Federal Office of Justice, ‹https://www.bundesjustizamt.de/EN/Topics/FederalCentralCriminalRegister/FederalCentralCriminalRegister_node.

በሀገራችን ያለው የሕግ ማዕቀፍም በውጪ ሀገር የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ እውቅና ሊሰጣቸው እንደሚችል ያሳያል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የወንጀል ህጉ የሚከተለውን ድንጋጌ ይዟል፡፡

> የተከሳሹን ያለፈ የህይወት ታሪክና ቅጣት የሚያከብዱ ምክንያቶችን፣ አመክሮ መስጠትንና ማስቀረትን፣ ደጋጋሚነትና የሚያስከትለውን ቅጣት፣ የደህንነት ማረጋገጫ እርምጃዎችን፣ ተከሳሽ በሕግ ፊት ችሎታ የሌለው መሆኑንና ከማዕረግ መሻርን፣ መሰየምን፣ የካሳ አከፋፈልን፣ የተወሰዱ እቃዎችን መመለስን፣ እና ሌሎች የፍትሃብሄር ነክነት ያላቸው ነገሮችን እንዲሁም በዚህ ሕግ ላይ የተደነገጉ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት በውጭ ሀገር ለተሰጠ ፍርድ እውቅናን መስጠት ይቻላል፡፡[20]

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው አንድ ተከሳሽ በውጭ ሀገር የነበረው የወንጀል ሪከርድ ለቅጣት ማክበጃነት በኢትዮጵያ ውስጥ ፋይዳ ሊኖረው እንደሚችል ነው፡፡ ህጉ በውጭ ሀገር የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ቅጣት ለማክበድ *ተቀባይት ሊኖራቸው ይገባል* በማለት አይደነግግም፡፡ ነገር ግን በውጭ ሀገር የተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ቅጣት ለማክበድ *እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል* በማለት ያስቀምጣል፡፡ በተጨማሪ በውጭ ሀገር ለተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች እውቅና መስጠትና በዚያው አግባብ ቅጣት ማክበድ የሚቻለው የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ተከሳሹ በውጭ ሀገር የተከሰሰበትና ጥፋተኛ የተባለበት ድርጊት በሀገራችን የወንጀል ሕግ መሰረትም እንደ ወንጀል የሚቆጠር መሆን አለበት፤ ፍርዱን የሰጠው የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት ልዩ ፍ/ቤት ሳይሆን መደበኛ ፍ/ቤት መሆን አለበት፤ ፍርዱ አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ባለስልጣን የተረጋገጠ መሆን አለበት፤ እና የፍርዱ ትክክለኛነት ስልጣን ባለው የውጭ ሀገር አካል የተረጋገጠ መሆን አለበት የሚሉ ናቸው፡፡[21] እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ጥምር በመሆናቸው ከእነርሱ መካከል አንዱ እንኳን ከጎደለ በውጭ ሀገር ለተሰጠ የጥፋተኛነት ውሳኔ በሀገራችን ፍ/ቤቶች እውቅና መስጠት አይቻልም፡፡

ከላይ የተሰጠው ማብራሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ በድጋሚ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች አንፃር የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ ውጤትን ስንመለከት በቀጥታ ለአዲሱ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት ሊያከብድ ይችላል፤ በሂደት ማቅለያ ሊያሳጣ ይችላል፤ ወይም ምንም ተፅእኖ ላይኖረው ይቻላል፡፡[22] ይህ ሁኔታ የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ እንደ ሀገሩ ምርጫ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ውጤቶች እንዲኖረው ሊያደረግ እንደሚቻል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

### ሀ. የቀደመ የወንጀል ታሪክ ውጤት አልባ መሆን አለበት

አንዳንድ ፀሃፊዎች እንደሚሉት የቀደመ የወንጀል ታሪክ (ሪከርድ) ወደፊት ለሚፈፀመው ወንጀል ቅጣት ማክበድ የለበትም፤ ይህ እንዲሆን ማድረግ አንድ ሰው ለአንድ ወንጀል ሁለት ጊዜ አይቀጣም የሚለውን መርህ ይጥሳል በማለት ከሰብዓዊ መብት አንፃር

html#:~:text=Convictions%20entered%20in%20the%20Federal,with%20the%20relevant%20legal%20provisions› accessed on 28 November 2023

[20] የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም፣ አንቀፅ 22(1) ይመልከቱ፡፡

[21] የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም፣ አንቀፅ 22(2) ይመልከቱ፡፡

[22] በዚህ ነጥብ ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት Mirko Bagaric, Punishment And Sentencing: A Rational Approach (Cavendish Publishing Limited CP, London and Sydney, 2001) 229-252 እና Julian V. Roberts, The Role of Criminal Record in the Sentencing Process (1997), 22 Journal of Crime and Justice, 303-362 ይመልከቱ፡፡

ይከራከራሉ፡፡[23] አንድ ሰው በሰራው ወንጀል ምክንያት የተጣለበትን ቅጣት ከጨረሰ በኋላ ሌላ ወንጀል በመስራቱ ምክንያት የሚጣልበት ቅጣት በመጀመሪያው ወንጀሉ ምክንያት እንዲጨምር የሚደረግ ከሆነ በጭማሪው ልክ ይህ ሰው ለመጀመሪያው ወንጀሉ ሁለተኛ ጊዜ እየተቀጣ ነው ማለት ነው፡፡[24] በእርግጥ ይህ ጭማሪ ወይም ድጋሚ ቅጣት በመጀመሪያው ወንጀል ምክንያት ለብቻው የሚጣል ሳይሆን ለሁለተኛው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመጀመሪያ ወንጀል ውጤት ማስገኘቱን (ቅጣት በማስጨመር) ቀጥሏል ማለት ሲሆን እንዲህ ዓይነት አካሄድ መሰረታዊ የሆነውን *አንድ ሰው ለአንድ ድርጊት ከአንድ ጊዜ በላይ አይቀጣም* የሚለውን መርህ አደጋ ላይ የሚጥል ይሆናል በማለት ይከራከራሉ፡፡[25]

በተጨማሪም ከቅጣት ጽንሰ ሀሳቦች ውስጥ አንዱ በሆነው ብቀላ (Retribution) መሰረት ቅጣት ማክበድ ተገቢ አለመሆኑን በማንሳት የሚከራከሩ ምሁራን አሉ፡፡[26] የብቃላ ጽንሰ ሀሳብ ቅጣት ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን የሚጠይቅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ የዚህ ጽንሰ ሀሳብ ቀንደኛ ደጋፊ ከሆኑ ፋላስፋዎች መካከል ኢማኑኤል ካንት *አንድ ሰው የሚቀጣው ወንጀል ስለፈፀመ ብቻ ሲሆን ተቀባይነት ያለው ቅጣትም ከተፈፀመው ወንጀል ጋር እኩል የሆነ ቅጣት ብቻ ነው* በማለት ይከራከራል፡፡[27] ስለዚህ በብቀላ ቅጣት ጽንሰ ሀሳብ እይታ በቀደመ የወንጀል ታሪክ ምክንያት ቅጣት የሚከብድ ከሆነ በወንጀሉ እና በቅጣቱ መካከል ሊኖር የሚገባው ተመጣጣኝነት ስለማይኖረው ከብዶ የሚጣል ቅጣት ተቀባይነት የለውም የሚል ሀሳብ አለ፡፡[28]

ስለሆነም *አንድ ሰው ለአንድ ድርጊት ከአንድ ጊዜ በላይ አይቀጣም* ከሚለውን ህገ-መንግስታዊ መርህ (prohibition of double jeopardy) እና ከብቀላ ቅጣት ጽንሰ መስፈርቶች አንፃር ሲታይ የቀደመ የወንጀል ታሪክ ለድጋሚ ወንጀል ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ ምንም ዓይነት ውጤት ሊኖረው አይገባም የሚል አንድ አቋም አለ፡፡

---

[23] Carissa Byrne Hessick and F. Andrew Hessick, Double Jeopardy as a Limit on Punishmen (2011) 97 Cornell L. Rev. 45, 45-86.

[24] እዚያው ይመልከቱ፡፡ If a defendant has already discharged the previous sentence of the court, is he not being sentenced a second time for the same criminal conduct? According to some jurists increased penalties because of prior crimes conflict with the principles underlying legal doctrines of double jeopardy. Many affirm that enhancing punishment for a recidivist nothing less than additional punishment for a prior offense. If an offender receives a much harsher penalty on the grounds that he has offended (and been punished) in the past, is this not punishment a second time for the same criminal conduct? If the offender remains law-abiding, no further penalty will ensue. However, in the event that a reconviction occurs, the previous crime will now have an effect, although that effect is hidden within a fresh sentence, as an enhancement rather than an independent disposition. See Julian V. Roberts, ከላይ በተ.ቁ. 22 የተጠቀሰ፣ ገፅ 316፡፡

[25] በሌላ በኩል *አንድ ሰው ለአንድ ድርጊት ከአንድ ጊዜ በላይ አይቀጣም* የሚለው መርህ መጨረሻ ላይ አንድ ወንጀለኛ የሚገባው ቅጣት ምን ያክል እንደሆነ በሚወሰንበት ጊዜ ተፈፃሚ አይሆንም የሚል እሳቤም አለ:: (The Double Jeopardy Clause does not apply at sentencing-the stage at a defendant's precise punishment is determined. ለበለጠ መረጃ፡ Carissa Byrne Hessick and F. Andrew Hessick, ከላይ በተ.ቁ. 23 የተጠቀሰ፣ ገፅ.45-86 ይመልከቱ፡፡

[26] በዚህ ነጥብ ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፡ Julian V. Roberts, ከላይ በተ.ቁ. 22 የተጠቀሰ፣ ገፅ 303-362 ይልከቱ፡፡ በተጨማሪ Andrew von Hirsch, The Project of Sentencing Reform in Michael Tonry and Richard S. Frase (ed), Sentencing and Sanctions in Western Countries (Oxford University Press, 2001) ከገፅ 405 ጀምሮ ይመልከቱ፡፡

[27] ለበለጠ መረጃ፡ Edmund L. Pincoffs, The Rationale of Legal Punishment (Humanities Press, New York, 1966) 4 ይመልከቱ፡፡

[28] እዚያው ይመልከቱ፡፡

**ለ. የቀደመ የወንጀል ታሪክ ቅጣት ማክበድ አለበት**

ከላይ ከተገለፀው አቋም በተቃራኒ አንድ ሰው ቀድሞ ከተቀጣ በኋላ በቀጣይ ለሚፈፅማቸው ወንጀሎች የሚጣሉ ቅጣቶች መከበድ አለባቸው (cumulative principle)፤ ምክንያቱም ይህ ሰው ከቀደመው ጥፋቱና ቅጣቱ አልተማረም ማለት ነው በማለት የሚከራከሩ አካላት አሉ፡፡[29] በእርግጥ በአሁን ጊዜ በሰዎች ዘንድ ደጋሚ ወንጀለኛ ከጀማሪ ወንጀለኛ የበለጠ ከፍ ያለ ቅጣት መቀጣት አለበት የሚል እሳቤ በስፋት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ይገኛል፡፡[30] ይህን አቋም የሚደግፉ ምሁራን ከቅጣት ፍልስፍና አንፃር ዲተረንስ (deterrence) እና ኢንከፓሲቴሽን (incapacitation) የሚባሉ ፅንሰ ሀሳቦችን በማንሳት ይከራከራሉ፡፡[31] እንደ እነርሱ ሀሳብ ከዲተረንስ አንፃር ሲታይ አንድ ቀድሞ የተቀጣ ሰው ከቀድሞ ቅጣቱ ተምሮ ከሌላ ወንጀል እራሱን መቆጠብ አለመቻሉ ወደፊት ሊፈፅም ከሚችለው ሌሎች ወንጀል እራሱን እንዲቆጥብ ለማድረግ ለሁለተኛ ወንጀሉ ከፍ ያለ ቅጣት መጠቀም የሚቻል ሲሆን ይህን ለማድረግ የቀደመ የወንጀል ታሪኩን (መማር አለመቻሉ) እንደ አንድ ምክንያት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ከኢንከፓሲቴሽን አንፃር የተወሰነ ጊዜ ነፃነቱ ተገድቦበት የተለቀቀ ሰው እንደ ገና ሌላ ወንጀል ከሰራ በድጋሚ ለፈፀመው ወንጀል ረዘም ላለ ጊዜ ነፃነቱ ተገድቦበት ተጨማሪ ወንጀል የመፈፀም እድሉ ሊጣበብበት ይገባል የሚል አቋም አለ፡፡

**ሐ. የቀደመ የወንጀል ታሪክ በሂደት ቅጣት ማቅለያ ማሳጣት አለበት**

ከላይ በተገለፁት ሁለት አቋሞች መካከል የሚገኝ ሌላ አቋም የቀደመ የወንጀል ታሪክ መኖር አንድ ሰው በድጋሚ ለሚፈፅማቸው ወንጀሎች የሚጣሉ ቅጣቶች እንዳይቀሉለት ሊያደርግ ይገባል (progressive loss of mitigation theory) እንጂ ቅጣት ሊያከብድ አይገባም የሚል ክርክር እና ሀሳብ አለ፡፡[32] ለምሳሌ በአውስትራሊያ ውስጥ በቀደመ ጥፋተኛነት መሰረት ለድጋሚ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት እንዲከብድ የሚደነግግ መርህ የለም፤ ነገር ግን ደጋሚ ወንጀለኛ እንደ ጀማሪ ወንጀለኛ ስለማይታዘንለት ከፍ ያለ ቅጣት ይጣልበታል፡፡[33] ይህ ሁኔታ ደጋሚ ጥፋተኛ በሀዘኔታ ማግኘት የሚችለውን ማቅለያ በሂደት እያጣ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በእርግጥ ማቅለያ ማጣት በራሱ ቅጣት ከፍ እንዲል የሚያደርግ ሁኔታ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ለምሳሌ ሁለት ሰዎች ተመሳሳይ ወንጀሎችን በተመሳሳይ ሁኔታ ቢፈፅሙ እና አንዱ ጀማሪ ወንጀለኛ እና ሌላው ደጋሚ ወንጀለኛ ቢሆኑ የቀደመ የወንጀል ታሪኩ ቅጣት ለማክበድ ከግምት ውስጥ ባይገባም ደጋሚ ወንጀለኛው የበለጠ ቅጣት እንደሚጣልበት ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም የደጋሚ ወንጀለኛው የቀደመ ባህሪው መልካም ነበረ ተብሎ ቅጣት እንዲቀልለት የሚያስደርግ ሁኔታ አይኖርም፡፡

---

[29] Julian V. Roberts, ከላይ በተ.ቁ. 22 የተጠቀሰ፣ ገፅ 303-362 ይመልከቱ፡፡
[30] Carissa Byrne Hessick and F. Andrew Hessick, ከላይ በተ.ቁ. 22 የተጠቀሰ፣ ገፅ 45-86 ይመልከቱ፡፡
[31] በዚህ ነጥብ ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፡ Julian V. Roberts, ከላይ በተ.ቁ. 22 የተጠቀሰ፣ ገፅ 303-362 ይመልከቱ፡፡
[32] እዚያው ይመልከቱ፡፡
[33] Mirko Bagaric, ከላይ በተ.ቁ. 22 የተጠቀሰ፣ ገፅ 230-231 ይመልከቱ፡፡

በአጠቃላይ የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ ውጤት በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ይመስላል፡፡ በሀገራችን የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነት ውጤቱ ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ቢሆንም ጥያቄው በኋላ በሌላ ክፍል ውስጥ በስፋት መልስና ማብራሪያ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ የቀደመ የወንጀል ታሪክ እንደ ቅጣት ማክበጃ ከመጠቀም አንፃር የተወሰኑ ሀገሮች ልምድ ይቃኛሉ፡፡

### 3.3. በሀገሮች ዘንድ የቀደመ የወንጀል ታሪክ እንደ ቅጣት ማክበጃ የመጠቀም ልምድ አጭር ምልከታ

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በአሁኑ ጊዜ ደጋሚ ወንጀለኛን በተመለከተ የቀደመ የወንጀል ታሪኩን/ሪከርዱን ለድጋሚ ወንጀሉ ቅጣት ማክበድ አለበት የሚል እሳቤ በስፋት ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑን በርካታ ሀገሮች የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ እንደ ቅጣት ማክበጃ ከሚጠቀሙባቸው ምክንያቶች መካከል የተከሳሹ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ወይም ታሪክ በዋናነት ተጠቃሽ ነው፡፡

ለምሳሌ በአሜሪካ የአንድን ሰው የቀደመ የወንጀል ታሪክ ወይም ሪከርድ እንደ ቅጣት ማክበጃ መጠቀም በጣም የቆየ ልምድ ነው፡፡[34] በዚህ ረገድ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአሜሪካ የቀደመ የወንጀል ታሪክ ወይም ሪከርድ እ.አ.አ. ከ1773 ጀምሮ በድጋሚ ለተፈፀመ ወንጀል ቅጣት ለመጨመር (ለማክበድ) ሲያገለግል ነበር፡፡[35] በተመሳሳይ ሁኔታ በደቡብ አፍሪካ የቀደመ የወንጀል ጥፋተኝነት ቅጣት ከሚያከብዱ ሁኔታዎች ውስጥ እንደ አንድ ተደርጎ በሕግ እውቅና ተሰጥቶታል፤[36] በህንድ የቀደመ የወንጀል ታሪክ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያት ነው፤[37] በካናዳ የወንጀል ሪከርድ መኖር ቅጣት እንዲጨምር የሚያደርግ ምክንያት ነው፤[38] በዩናይትድ ኪንግደም ምክንያታዊ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የተከሳሽ የቀደመ ወንጀል ሪከርድ ለአዲስ ወንጀል የሚጣለውን ቅጣት እንዲያከብድ ተግባራዊ መደረግ አለበት፤[39] ወዘተ፡፡

የቀደመ የወንጀል ታሪክን እንደ ቅጣት ማክበጃ ከመጠቀም አንፃር ከላይ የተጠቀሱት ሀገሮች አቋም ከቅጣት ፍልስፍና ወይም ጽንሰ ሀሳቦች መካከል በዲተረንስ (deterrence) ወይም በኢንከፓሲቴሽን (incapacitation) የሚደገፍ ሊሆን ይችላል፡፡

---

[34] Kevin R. Reitz, The Disassembly and Reassembly of U.S. Sentencing Practices in Michael Tonry and Richard S. Frase (eds), Sentencing and Sanctions in Western Countries, (Oxford University Press, 2001) 229; Aggravating Factor, ከላይ በተ.ቁ. 12 የተጠቀሰ፡፡ በአሜሪካ አንድ ሰው ሁለት ቀላል ወንጀሎችን ከፈፀመ በኋላ ለሶስተኛ ጊዜ ቀላል ወንጀል ቢፈፅም ይህ ሶስተኛው ቀላል ወንጀል ረጅም የእስራት ቅጣትን ሊያስከትልበት ይችላል (three strikes law)፤ ምክንያቱም የቀደሙት ጥፋተኝነቶቹ ቅጣቱን ስለሚያከብዱበት ነው፡፡ Yash Jain, ከላይ በተ.ቁ. 15 የተጠቀሰ ይመልከቱ፡፡ በአጠቃላይ በአሜሪካ የቀደመ የወንጀል ታሪክ እ.አ.አ. ከ1773 ጀምሮ ቅጣት ለመጨመር ሲያገለግል እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ The Impact of Prior Criminal Convictions, ‹https://www.justcriminallaw.com/criminal-charges-questions/2020/02/26/impact-prior-criminal-convictions/› accessed on 28 November 2023.

[35] እዚያው ይመልከቱ፡፡

[36] በዚህ ነጥብ ላይ ለበለጠ መረጃ እ.አ.አ. ከ 01 October 2019 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነ በ "Sentencing Guidelines Council" የተዘጋጀ የደቡብ አፍሪካ General guideline: overarching principles, ከላይ በተ.ቁ. 14 የተጠቀሰ ይመልከቱ፡፡

[37] በዚህ ነጥብ ላይ ለበለጠ መረጃ Yash Jain, ከላይ በተ.ቁ. 15 የተጠቀሰ ይመልከቱ፡፡.

[38] How Sentences are imposed, Government of Canada, ከላይ በተ.ቁ. 11 የተጠቀሰ ይመልከቱ::

[39] Previous Convictions, ‹https://www.sentencingacademy.org.uk/previous-convictions/#:~:text=Where%20offenders%20have%20previously%20been,'reasonable'%20to%20do%20so› accessed on 28 November 2023.

የእነዚህ ፍልስፍናዎች አቋም አንድ ሰው መቀጣት ያለበት ባደረሰው ጉዳት ልክ ነው የሚል ሳይሆን የቅጣቱ መጠን መወሰን የሚገባው ከቅጣት ዓላማ አንፃር መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ወንጀለኞች በመጀመሪያው ቅጣታቸው ካልተማሩ ሌላ ከፍ ያለ ቅጣት ሊያስተምራቸው ስለሚችል ለድጋሚ ወንጀላቸው ቅጣታቸው መክበድ እንዳለበት ከዲተረንስ ፍልስፍና እንረዳለን፤ እንዲሁም ለቀደመው ወንጀላቸው የደረሰባቸው ጉዳት (ቅጣት) ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈፅሙ እድል ካልነፈጋቸው ለድጋሚ ወንጀላቸው የበለጠ እድል የሚያጣብብ ቅጣት ማክበጃን በመጠቀም መጣል አለበት የሚለው ከኢንከፓሲቴሽን ፍልስፍና እንረዳለን፡፡ ስለዚህ የሚከተሉት የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ ዲተረንስም ይሁን ኢንከፓሲቴሽን በርካታ ሀገሮች የቀደመ የወንጀል ሪከርድን የቅጣት ማክበጃ ሰበብ አድርገው እየተጠቀሙበት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 3.4. የቀደመ የወንጀል ታሪክ ውጤትን አስመልክቶ በሀገራችን ያለው ሁኔታ

በዚህ ፅሁፍ በመግቢያ ክፍል ውስጥ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በሀገራችን ያለው ልማድ አንድ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ያለበት ከሆነ በዐ/ሕግ በኩል በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1(ሐ)) መሰረት ለድጋሚ ወንጀሉ የሚወሰነው ቅጣት እንዲከብድ የቅጣት አስተያየት በመደበኛነት ይቀርባል፤ የወንጀል ሪከርድ መኖሩ ትክክል ከሆነ ቅጣቱም ይከብዳል፡፡ ይህ በፍ/ቤቶች አካባቢ በብዛት የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ነገር ግን *እንደዚህ ዓይነት አካሄድ ትክክል ነው ወይ?* የሚለውን ጥያቄ ማንሳት እና መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ *በወንጀል ህጋችን መሰረት በቀደመ የወንጀል ሪከርድ መሰረት ቅጣትን ማክበድ የሚቻለው መቼ ነው?* ብሎ መጠየቅ እና መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ ለተነሳው ጥያቄ ከህጉ አንፃር ትንታኔ ከማቅረብ በፊት የሕግ ባለሙያዎች አቋም ምን እንደሚመስል ማየት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የፖል ጥያቄ[40] በቴሌግራም (በ17/01/2016 ዓ.ም.) እና በፌስቡክ (በ15/01/2016 ዓ.ም.) ተለቋል፡፡ ለጥናት መረጃ ለማሰባሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም የሚቻል ሲሆን ከእነዚህ መካከል መጠይቅ መበተን እና ቃለ-መጠይቅ ማድረግ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንዲሁም ጥያቄዎችን ለተጠያቂዎች በአካል መስጠት፣ በስልክ ማቅረብ፣ እና በኢሜል መላክ የሚቻል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በቴሌግራም እና በፌስቡክ ጥያቄ ለመረጃ ሰጪዎች መላክ የጊዜ መሻሻል ያስገኘው ዘዴ ጥቅም ላይ መዋሉን የሚያሳይ እንጂ በጥናት ስልት የማይፈቀድ አካሄድ አይደለም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ መረጃ አግባብነት ካላቸው ባለሙያዎች ለማግኘት የፖል ጥያቄ በቴሌግራም እና በፌስቡክ መላክ (መልቀቅ) አስፈላጊ ያደረጉት ብዙ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ አንደኛ ዘዴው በጥያቄው ላይ መረጃ በመስጠት በርካታ የሕግ ባለሙያዎች እንዲሳተፉበት የሚያስችል ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ የመረጃ ሰጪዎች ቁጥር ከፍ ማለት የጥናት ውጤት ተዓማኒነት ከሚጨምሩ ምክንያቶች መካከል አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ሀቅ ነው፡፡ ሁለተኛ ዘዴው በየትኛውም ቦታ (በሀገር ውስጥ እና ከሀገር በውጪ) የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ እና መረጃ እንዲሰጡ የሚያስችል ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ በተለመደው አሰራር ተደራሽ ሊሆኑ የሚችሉት ሰዎች በቅርበት ያሉት ብቻ ናቸው፡፡ ሶስተኛ ዘዴው ተሳታፊዎች በቀላሉ ስልካቸውን ብቻ በመጠቀም ለጥናት የሚሆን መረጃ እንዲሰጡ ስለሚያስችል ነው፡፡ አራተኛ ይህ ዘዴ በስራ መብዛት እና በሌሎች ምክንያቶች በቀላሉ ሊገኙ እና መረጃ ሊሰጡ ከማይችሉ ሰዎች

[40] ለህግ ባለሙያዎቹ የቀረበው የፖል ጥያቄ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84 ድንጋጌ እና በእውነተኛ የፍ/ቤት ጉዳይ (አሰራር) ላይ በመመስረት የተዘጋጀ "hypothetical" ጥያቄ ነው፡፡

መረጃ እንዲገኝ የሚያስችል ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ አምስተኛው ዘዴው ተሳታፊዎች በሚመቻቸው ጊዜ (ቀን፣ ማታ፣ ወዘተ) መረጃ እንዲሰጡ የሚያስችል ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ ስድስተኛ ዘዴው ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ለመጠቀም ቀላል ሆነ መገኘቱ ነው፡፡ የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መረጃ በቴሌግራም እና በፌስቡክ እንዲሰበሰብ አድርጓል፡፡ ነገር ግን በቴሌግራም እና በፌስቡክ የሚሰበሰበው መረጃ ተዓማኒ እና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ጥያቄ በሕግ ባለሙያዎች ብቻ እንዲመለስ ማድረግ የግድ ስለነበረ የተዘጋጀው ጥያቄ የተላከው (የተለቀቀው) ለህዝብ ሳይሆን ለሕግ ባለሙያዎች ብቻ ነበር፡፡ በመሆኑም የሕግ ባለሙያ ሳይሆን በቀረበው ጥያቄ መሰረት መረጃ እንዲሰጥ የተደረገ ሰው የለም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፖል ጥያቄው በቴሌግራም እና በፌስቡክ ከተለቀቀ በኋላ ለጥያቄው መልስ በመስጠት በአጠቃላይ 211 የሕግ ባለሙያዎች (ዳኞች፣ ዐ/ህጎች፣ ጠበቆች፣ የሕግ መምህራን፣ ነገረ ፈጆች፣ ወዘተ) ተሳትፎ አድርገው አቋማቸውን ገልፀዋል፡፡ ጥያቄው እና የተገለጸው አቋም የሚከተለው ነው፡፡

> አንድ ሰው ሁለት ወንጀሎችን በተለያየ ጊዜ ከፈፀመ በኋላ በአንዱ ተወስኖበት በእስር ላይ እያለ ለቀሪው ወንጀል ሌላ ጊዜ ተከስሶ (በኋላ ስለተደረሰበት) ጥፋተኛ ቢባል ቀድሞ በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ/ሪከርዱ በወንጀል ህጉ መሰረት ለሁለተኛ ወንጀሉ ቅጣቱን ሊያከብድ ይችላል?

ተሳታፊ ባለሙያዎች በወንጀል ህጉ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እና በተግባር ያጋጣማቸውን ልምድ በመጠቀም ለጥያቄው መልስ እንዲሰጡ የተጠየቁ ሲሆን የተገኘው መልስ እኩል ሊባል በሚችል ደረጃ የተከፋፈለ ነው፡፡ ለምሳሌ በቴልግራም መልስ የሰጡ የሕግ ባለሙያዎች ብዛት 183 ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል 90 ባለሙያዎች (49.2%) የሚሆኑት ከላይ በተገለፀው አግባብ የቀደመ የወንጀል ታሪክ *ቅጣት ሊያከብድ አይችልም* ሲሉ 87 (47.5%) ባለሙያዎች ደግሞ *ቅጣቱ ሊከብድ ይችላል* ብሏል፡፡ 6 ባለሙያዎች (3.3%) ባለሙያዎች መልሱ ምን መሆን እንዳለበት እርግጠኞች እንዳልሆኑ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው አንዱም አቋም ከግማሽ በላይ (50%) ደጋፊ ያላገኘ መሆኑን ነው፡፡

በተመሳሳይ መልክ ጥያቄው በፌስቡክ ዝግ በሆነ መንገድ ለ89 የሕግ ባለሙያዎች ከቀረበ በኋላ ጥያቄውን ከተመለከቱት 75 ባለሙያዎች መካከል 28ቱ ብቻ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በተሰጠው መልስ መሰረትም በጥያቄው ላይ በተገለፀው አግባብ የቀደመ የወንጀል ታሪክ *ቅጣት ሊያከብድ ይችላል* ያሉት የሕግ ባለሙያዎች 17(60.7%) ሲሆኑ የቀደመ የወንጀል ታሪክ *ቅጣት ሊያከብድ አይችልም* ያሉት የሕግ ባለሙያዎች ደግሞ 11(39.3%) ናቸው፡፡ በቴሌግራም ከተሰበሰበው መረጃ ይልቅ በፌስቡክ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የአቋም ልዩነት ሰፊ መሆኑን መረዳት የሚቻል ሲሆን ይህም ሁለት ወንጀሎችን በተለያየ ጊዜ የፈፀመ ሰው ለአንዱ ወንጀል በመጀመሪያ የተጣለበትን ቅጣት እየፈፀመ እያለ ለቀረውም ወንጀልም ጥፋተኛ ከተባለ ቀድሞ ጥፋተኛ መባሉ ለሁለተኛው ወንጀሉ የሚጣልበትን ቅጣት ሊያከብድበት ይችላል የሚል አቋም የበለጠ ደጋፊ ያገኘ አቋም ነው፡፡

ነገር ግን በቴሌግራም እና በፌስቡክ መረጃ የሰጡ የሕግ ባለሙያዎችን አንድ ላይ ተደምረው ሲታዩ አጠቃላይ ቁጥራቸው 211 ይሆናል፡፡ ከእነዚህ 211 ባለሙያዎች መካከል ከላይ በጥያቄ ውስጥ በተገለፀው ሁኔታ የቀደመ የወንጀል ታሪክ ቅጣት ሊያከብድ

*ይችላል ያሉት* ብዛታቸው 104 (49.3%) ሲሆኑ *አይችልም ያሉት* ደግሞ 101 (47.9%) ናቸው፤ 6 (2.8%) ባለሙያዎች ስለመልሱ እርግጠኞች አለመሆናቸውን የገለፁ ናቸው፡፡ ስለዚህ የአቋም ልዩነቱ ከሞላ ጎደል በእኩል ደረጃ የተከፋፈለ መሆኑን እና ባለሙያዎቹ በብዛት የሚስማሙበት አንድ አቋም አለመኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

በጉዳዩ ላይ በባለሙያዎች ዘንድ ያለው ግንዛቤ ከላይ የተጠቀሰውን እውነታ የሚያሳየው ከሆነ ትክክለኛው የወንጀል ህጉ አቋምስ ምንድን ነው የሚለውን ከህጉ አንፃር መተንተን አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከተጠየቀው ጥያቄ አንፃር የወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ ላይ በዚህ ደረጃ በባለሙያዎች መካከል የአቋም ልዩነት መኖሩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በተመሳሳይ ጉዳዩ ላይ ባለሙያዎች መከተል የሚገባቸው አቋም የትኛው መሆን እንዳለበት ከሕግ ድንጋጌ አንፃር ማስቀመጥ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል፡፡

ምክንያቱም የቀደመ የወንጀል ሪከርድ እንደ ቅጣት ማክበጃ ማገልገል በሚገባው ጊዜ እንደ ቅጣት ማክበጃ አለመጠቀም ወንጀለኛ በተባለ ሰው ላይ መጣል ያለበት ቅጣት እንዳይጣል ያደርጋል፣ ይህ ደግሞ የቅጣት ዓላማ መሳካት ላይ የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል የቀደመ የወንጀል ሪከርድ እንደ ቅጣት ማክበጃ ማገልገል ከሌለበት ሁኔታውን እንደ ቅጣት ማክበጃ መጠቀም ጥፋተኛ የተባለ ሰው ላይ አላስፈላጊ ቅጣት እንዲጣልበት ያደርጋል፤ ይህ የህጋዊነት መርህን የሚፃረር እና ለቅጣት ዓላማ መሳካትም አስተዋፅኦ የማይኖረው ይሆናል፡፡ በመሆኑም የወንጀል ህጋችን በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው አቋም ምንድን ነው የሚለው ከድንጋጌው እና ከመንፈሱ አንፃር መቃኘት አስፈላጊ ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ ሰፊ ትንታኔ ቀርቧል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በሀገራችን የቀደመ የወንጀል ታሪክ ወይም ሪከርድ *በአራት መንገድ* ጠቀሜታ/ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ከወንጀል ህጉ የተለያዩ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ጠቃሜታዎች ወይም ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

አንደኛው የቀደመ የወንጀል ሪከርድ በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ ለተባለ ሰው ቅጣት እንዳይቀልለት ያደርጋል፡፡ ይህ የቀደመ የወንጀል ታሪክ/ሪከርድ *አለመኖር* ውጤት አልባ (neutral) አለመሆኑን ያሳያል፡፡ የሪከርድ አለመኖር በህጉ አንቀፅ 82(1)(ሀ) መሰረት የወንጀለኛው የቀደመ ባህሪው መልካም ነበር የሚል ግምት ስለሚያስወስድ ለጀማሪ ወንጀለኛ ቅጣት እንዲቀል የሚያደርግ ሁኔታ ነው፡፡[41] የቀደመ የወንጀል ታሪክ መኖር ግን ይህን ግምት የሚያፈርስ በመሆኑ ቅጣት እንዳይቀል ያደርጋል፡፡ ይህ ውጤት የወንጀል ህጉ የቀደመ የወንጀል ታሪክ መኖር የጥፋተኛው የቀድሞ ባህሪው መልካም ነበር ተብሎ ቅጣት እንዳይቀል የማድረግ ውጤት ሊኖረው ይገባል ለሚለው እሳቤ (progressive loss of mitigation theory) ቦታ የሰጠ መሆኑን ያሳያል፡፡
በሁለተኛ ደረጃ የቀደመ የወንጀል ታሪክ መኖሩ የተወሰኑ አስፈላጊ መስፈርቶች ከተሟሉ ወንጀለኛውን ደጋጋሚ[42] ስለሚያሰኙት የጥፋተኛነት ታሪኩ/ሪከርዱ እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ሊያገለግ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው የወንጀል ህጉ አንቀፅ 67 መስፈርቶች

[41] የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም. አንቀፅ 82(1)(ሀ) ይመልከቱ፡፡
[42] በወንጀል ህጋችን መሰረት ወንጀልን ከአንድ ጊዜ በላይ የፈፀመ ሰው ደጋጋሚ ተብሎ ይጠራል፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም. አንቀፅ 67 ይልከቱ፡፡ ነገር ግን በዚህ ፀሃፊ ዕይታ *ደጋጋሚ* ለማለት አንድ ሰው ቢያንስ ሶስት ጊዜ ወንጀል መስራት አለበት፡፡ ለሁለተኛ ወንጀሉ *ደጋሚ* የሚል ቃል መጠቀም የበለጠ አግባብነት ያለው ይመስላል፡፡

ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ በአንቀፅ 67 መሰረት አንድ ሰው ደጋጋሚ ተብሎ እንዲቆጠር እና የቀድሞ የወንጀል ታሪኩ እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ እንዲያገለግል አዲሱ ወንጀል ቢያንስ በስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ መሆን እንዳለበት፣ የተፈፀመው አዲስ ወንጀል ሆን ተብሎ የተፈፀመ መሆን እንዳለበት፣ አዲሱ ወንጀል የተፈፀመው ወንጀለኛው የቀድሞ ቅጣቱን በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመ ወይም በይቅርታ ከቀረለት ቀን ጀምሮ በ5 ዓመት ውስጥ ከሆነ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ መስፈርቶች ከተሟሉ የቀደመ የወንጀል ታሪክ እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ውጤት የሚኖረው ይሆናል፡፡[43]

በሶስተኛ ደረጃ የቀደመ የወንጀል ታሪክ በወንጀል ህጋች አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሚያገለግል ነው፡፡ ህጉ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎችን በሚዘረዝርበት ጊዜ **ወንጀለኛው በቀድሞ ጥፋተኛነቱ** ምክንያት **የተለየ አደገኛነቱ የሚታይ** ከሆነ ቅጣቱ ሊከብድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ወንጀለኛ በህጉ አንቀፅ 67 መሰረት ደጋጋሚ የማይባል ከሆነ የቀደመ የወንጀል ታሪኩ በአንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ቅጣትን ሊያከብድ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ቀድሞ ተቀጥቶ የነበረ ሰው እንደገና ሌላ ወንጀል መስራት አደገኛነቱን የሚያሳይ በመሆኑ ቅጣቱ የበለጠ አስተማሪ እንዲሆን የተጨመረ/የከበደ መሆን ይኖርበታል፡፡

በአራተኛ ደረጃ የቀድሞ ጥፋተኛነት ታሪክ ወይም ሪከርድ ውጤት አልባ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው የጥፋተኛነት ሪከርድ እንዲሰረዝ ወይም ቀሪ እንዲሆን የሚያደርጉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ምህረት ነው፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 230(2) ስር እንደሚደነግገው *ምህረት በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ ቅጣት ተወስኖ እንደሆነ ምህረቱ ቅጣቱንና ቅጣቱ የሚያስከትለውን ማንኛዎቹንም ሌሎች የወንጀል ውጤቶች ያስቀራል፤ የጥፋተኛነት ውሳኔም እንዳልነበረ ተቆጥሮ ከወንጀለኞች መዝገብ ላይ ይሰረዛል፡፡* ከዚህ ድንጋጌ አንድ ቀድሞ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የነበረ ሰው ምህረት ከተሰጠው አንዳችም የቀደመ የወንጀል ሪከርድ የሌለበት ሰው ተደርጎ የሚቆጠር እንደሆነ መረዳት ይቻለል፡፡ ስለዚህ በወንጀለኞች ባህር መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የነበረ ወንጀለኛ ከመዝገቡ ላይ ስሙ እና ሪከርዱ ስለሚሰረዝ ለወደፊት ሌላ ወንጀል ቢሰራ እንደ ጀማሪ ወንጀለኛ የሚቆጠር ይሆናል፡፡ በመሆኑም የቀደመ የወንጀል ጥፋተኛነቱ እንደ ሪከርድ በማገልገል ቅጣቱን የሚያከብድበት አግባብ አይኖረውም፡፡

ሌላው የቀድሞ የጥፋተኛነት ታሪክን/ሪከርድን ውጤት አልባ የሚያደርገው ሁኔታ መሰየም (reinstatement) ነው፡፡ አንድ ቀድሞ ጥፋተኛ ተብሎ የነበረ ሰው ከመቀጣቱ በፊት የነበረው መልካም ስሙ እንዲመለስለት እና የተላለፈበት ፍርድ እንዲሰረዝለት በሚያቀርበው አቤቱታ መሰረት በፍ/ቤት ሊሰየም ይችላል፡፡[44] በእርግጥ መሰየም በመልካም ስራ የሚገኝ እንጂ ሙብት አይደለም፤[45] እንዲሁም የመሰየም ጥያቄ በፍ/ቤት ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው መሟላት የሚገባቸው በርካታ መስፈርቶች አሉ፡፡[46] አመልካቹ አስፈላጊውን መስፈርቶች ማሟላቱን እና ለመሰየም የሚያበቃው መልካም ስራ የነበረው መሆኑ

---

[43] እዚያው አንቀፅ 67 እና 188 ይመልከቱ፡፡
[44] እዚያው አንቀፅ 232 ይመልከቱ፡፡
[45] እዚያው አንቀፅ 232 ይመልከቱ፡፡
[46] እዚያው አንቀፅ 233 ይመልከቱ፡፡

በፍ/ቤት ሲረጋገጥ የመሰየም ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የመሰየም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ከሚያስከትላቸው ውጤች መካከል አንዱ የቀድሞ የወንጀል ታሪክ እንዳልነበረ ማድረግ ነው፡፡[47] ስለዚህ አንድ የተሰየመ ሰው እንዲሰየም ከተፈቀደለት ጊዜ አንስቶ ከአምስት ዓመት በኋላ[48] ሌላ ወንጀል ከፈፀመ የቀደመ የወንጀል ታሪኩ እንዳልነበረ ስለሚቆጠር ምንም ውጤት አይኖረውም፡፡ ይህ የተሰየመ ሰው የድሮ የወንጀል ታሪኩ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 67 ወይም አንቀፅ 84 ወይም አንቀፅ 86 መሰረት ውጤት ሊኖረው እንደማይችል ያሳያል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ውጤቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሕግ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ከተደረገው ጥያቄ አንፃር በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ቅጣት መከበድ አለበት ወይ? የሚለውን ነጥብ አሁን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ ጥያቄውን ለማስታወስ ያክል *“አንድ ሰው ሁለት ወንጀሎችን በተለያየ ጊዜ ከፈፀመ በኋላ በአንዱ ተወስኖበት በእስር ላይ እያለ ለቀሪው ወንጀል ሌላ ጊዜ ተከስሶ (በኋላ ስለተደረሰበት) ጥፋተኛ ቢባል ቀድሞ በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ/ሪከርዱ በወንጀል ህጉ መሰረት ለሁለተኛ ወንጀሉ ቅጣቱን ሊያከብድ ይችላል?”* የሚል ነው፡፡

በመጀመሪያ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት አንድ ሰው በቀድሞ ጥፋተኛነት ምክንያት በተለየ ሁኔታ አደገኛ ነው ሊባል የሚችል ከሆነ ብቻ ቅጣቱ ሊከብድ እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው ቀድሞ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ከተቀጣ በኋላ **በተለየ ሁኔታ አደገኛ ነው** ሊባል የሚችለው ይህን (የመጀመሪያውን) ቅጣት ጨርሶ ከወጣ በኋላ ከቅጣቱ ሳይማር ቀርቶ ሌላ ወንጀል የሰራ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ቅጣቱ አስተምሮት ሕግ አክባሪ ሆኖ እየኖረ ያለ ሰው ከመቀጣቱ በፊት ፈፅሞት የነበረ ወንጀል ስለተደረሰበት እንደገና ቢከሰስ እና ጥፋተኛ ቢባል ቀድሞ ተጥሎበት የነበረው ቅጣት እንዳላስተማረው ተወስዶ **በተለየ ሁኔታ አደገኛ ነው**[49] ተብሎ ቅጣቱ የሚከብድበት ምክንያት የለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለመጀመሪያው ወንጀሉ ቅጣት ተጥሎበት ቅጣቱን እየፈፀመ ያለ ሰው ቅጣቱን ፈፅሞ ሳይጨርስ ቀድሞ ፈፅሞ የነበረው ሌላ ወንጀል ከተደረሰበት በዚህ ወንጀል ምክንያት በሚቀጣበት ጊዜ የቀድሞ ጥፋተኛነቱ እንደ ቅጣት ማከበጃ ሊያገልግል አይገባም፡፡

በአጠቃላይ ከወንጀል ሕጉ መንፈስ ስንነሳ የቀደመ የወንጀል ታሪክ እንደ ጠቅላላ ቅጣት ማከበጃ ሊያገለግል የሚገባው ወንጀለኛ ቀድሞ ለፈፀመው ወንጀል ተጥሎበት የነበረው ቅጣት ከጨረሰ በኋላ ከቅጣቱ ሳይማር ቀርቶ ሌላ ወንጀል ከሰራ ነው፡፡[50] አንድ ሰው ተጥሎበት የነበረውን ቅጣት ከጨረሰ በኋላ ሌላ ወንጀል ከሰራ የቀደመው ቅጣት በአግባቡ አላስተማረውም ሊባል የሚችል ነው፡፡[51] በመሆኑም በድጋሚ ለተፈፀሙ ወንጀሎች የሚጣሉ ቅጣቶች ትምህርት ሰጪ እንዲሆኑ ከፍ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

---

[47] እዚያው አንቀፅ 235(2) ይመልከቱ፡፡

[48] አመልካቹ እንዲሰየም ከተፈቀደለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ ሌላ በሞት ወይም በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ከፈፀመ የተፈቀደለት መሰየም የሚሰረዝ እና ከዚያ በኋላ እንደገና ሊሰየም እንደማይችል ህጉ ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ህግ አንቀፅ 237 ይመልከቱ፡፡

[49] አንድ ወንጀለኛ በተለየ ሁኔታ አደገኛ መሆኑን ያሳያል ተብሎ በወንጀል ሕጉ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች መካከል አንዱ የቀድሞ ጥፋተኛነት መኖር ነው፡፡ እዚያው አንቀጽ 84(፣)(ሐ)ን ይመልከቱ፡፡

[50] አንዳንድ ሰዎች በፈፀሙት ወንጀል የማይፀፀቱ እና ከተጣለባቸው ቅጣት የማይማሩ አደገኞች ናቸው፡፡

[51] በእርግጥ ሰዎች ወንጀል የሚፈፅሙባቸው በርካታ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ወንጀልን ከአንድ ጊዜ በላይ ከፈፀመ ወንጀል መድገሙ አደገኛነቱን እንደማያሳይ በማስረዳት የቀድሞ ሪከርዱ ቅጣት እንዳያከብድበት ሊከራከር ይችላል፤ ይገባል፡፡

ከላይ ከተገለፀው ሁኔታ ውጪ በመሆን አንድ ሰው ተቀጥቶ ቅጣቱን በመፈፀም ላይ እያለ በሌላ ወንጀል ቢከሰስ እና ጥፋተኛ ቢባል የቀደመ ታሪኩ (ጥፋተኛ መባሉ) እንደ ቅጣት ማክበጃ ተግባራዊ ሊሆን አይገባም፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው ቀድሞ ከተጣለበት ቅጣት ባለመማሩ አዲሱ ቅጣቱ ከፍ መደረግ አለበት ሊባል ስለማይችል ነው፡፡

በተጨማሪ የወንጀል ሪከርድ እንደ ቅጣት ማክበጃ ሊያገለግል የሚገባው አንድ ሰው ከተቀጣ በኋላ ለሚፈፅመው ወንጀል ነው እንጂ ከመቀጣቱ በፊት ለፈፀማቸው ወንጀሎች ሊሆን አይገባም፡፡ ወንጀለኛው ከመያዙ እና ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት የፈፀማቸው ወንጀሎች ካሉ እነዚህ ወንጀሎች እንደ አስፈላጊነቱ በተደራራቢነት የሚታዩበት ሁኔታ ሊኖር ይችል ይሆናል[52] እንጂ ከቀደመው የወንጀል ታሪክ (የወንጀል ሪከርድ) ጋር መገናኘት የለባቸውም፡፡

የወንጀሎች ተደራራቢነት እንደ ቅጣት ማክበጃ ለመጠቀም ሁኔታዎች የማይፈቅዱ ከሆነ ያለው ብቸኛው አማራጭ ለተፈፀሙ እያዳንዱ ወንጀሎች በቅጣት አወሳሳን መመሪያ መሰረት ቅጣት መወሰን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ መውጣት የህጋዊነት መርህ መጣስ የሚያስከትል መሆኑ ከግምት ሊገባ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በህጋዊነት መርህ መሰረት ህጉ የማይፈቅደውን የቅጣት ማክበጃ መጠቀም ቅጣትን አመሳስሎ እንደመፍጠር (Creation of Penalty by Analogy) የሚቆጥር ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ ከተሰጠው ማብራሪያ አንፃር ሲታይ ለቀረበው የፖል ጥያቄ መልስ ከሰጡት 211 የሕግ ባለሙያዎች መካከል 104(49.3%) የሚሆኑን የሰጡት ሀሳብ ወይም የገለፁት አቋም አሳማኝ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን ከግማሽ በታች ቢሆኑም 101(47.9%) የሕግ ባለሙያዎች የሰጡት ሀሳብ ወይም የገለፁት አቋም የበለጠ አሳማኝ እና የህጉን መንፈስ የተከተለ ነው ብሎ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በጉዳዩ ላይ አቋም የለንም ያሉት 6(2.8%) ባለሙያዎች ደግሞ 101(47.9%) የሚሆኑ የሕግ ባለሙያዎች የሰጡት መልስ የበለጠ አሳማኝ እና የህጉን መንፈስ የተከተለ በመሆኑ በዚሁ አግባብ አቋማቸውን ግልፅ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

በተግባር ከሚታየው ሁኔታ አንፃርም በፍ/ቤት አካባቢ አብላጫው መልስ ሰጪ (104(49.3%)) የያዘውን አቋም የመውሳድ እና የመሳሳት አዝማሚያዎች ይታያሉ፡፡ በዚህ ረገድ የሚከተለው እውነተኛ የፍ/ቤት ጉዳይ ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ ተከሳሽ አቶ ደጀኔ ፍቃዱ በቀለ በተለያየ ጊዜ በቂ ስንቅ የሌላቸውን ቼኮችን ለሰዎች ሰጥቷል ተብሎ በከሳሽ የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ በሁለት ፍ/ቤቶች (በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እና በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት) ክስ የቀረበበት ሲሆን በአንደኛው (በአራዳው ፍ/ቤት) ክስ ቀድሞ የሶስት ዓመት ከሰባት ወር እስራት ተፈርዶበት ነበር፡፡ ከዚያም አቶ ደጀኔ ፍቃዱ በቀለ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት እየፈፀመ ባለበት ሁኔታ በሌላ ፍ/ቤት (በቦሌው ፍ/ቤት) ሲከታተል በነበረው

[52] የተፈፀሙ ወንጀሎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 60 እና ከአንቀፅ 64-66 ያሉ ድንጋጌዎች መስፈርቶችን በማሟላት ተደራራቢ ሊባሉ ከቻሉ የወንጀሎቹ መደራረብ እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ወይም 187 መሰረት ሊታይ ይችላል፡፡

ተመሳሳይ በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ የመስጠት ወንጀልም ጥፋተኛ ተባለ፡፡ በዚህ መሰረት የቅጣት አስተያየት እንዲቀርብ ጉዳዩን ከያዘው የቦሌው ምድብ ችሎቱ በተጠየቀው ጊዜ በዐ/ሕግ በኩል ቀርቦ የነበረው አንደኛው የቅጣት ሀሳብ ተከሳሽ ከዚህ ቀደም በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በመስጠት በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ጥፋተኛ ተብሎ በእስር ላይ ስለሚገኝ አሁን በድጋሚ ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት በወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ሊከብድ ይገባል የሚል ነበር፡፡ ጉዳዩን የያዘው ችሎትም ይህን የዐ/ሕግ የቅጣት አስተያየት በመቀበል የአቶ ደጀኔ ፍቃዱ በቀለ ቅጣት በአንድ እርከን ከፍ እንዲል አድርጎ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡[53]

ከላይ በተገለፀው አግባብ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ/ጥፋተኛነት ቅጣት ሊያከብድ አይገባም ነበር፡፡ ምክንያቱም ተከሳሹ አቶ ደጀኔ ፍቃዱ የመጀመሪያ ቅጣቱን እየፈፀመ የሚገኝ ግለሰብ እንጂ ቅጣቱን ጨርሶ ከወጣ በኋላ ከቅጣቱ ሳይማር ቀርቶ ሌላ ወንጀል የፈፀመ ሰው አልነበረም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የአቶ ደጀኔ ፍቃዱ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ በምንም አግባብ የተለየ አደገኛነቱን ሊያሳይ ስለማይችል የወንጀል ህጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መስፈርት ሊሟላ አይችልም፡፡ የወንጀል ሕግ አንድ ሰው በቀደሞ ጥፋተኛነቱ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ ከሆነ ቅጣቱ ሊከብድ ይችላል ብሎ ሲደነግግ ቀድሞ ተጥሎበት የነበረውን ቅጣት ከፈፀመ በኋላ ሳይማር ቀርቶ ወይም ለቀድሞ ቅጣቱ ቦታ ሳይሰጠው ሌላ አዲስ ወንጀል የፈፀመውን ሰው ታሳቢ የሚያደርግ እንጂ እንደ አቶ ደጀኔ ፍቃዱ ያሉ ተከሳሾችን የሚመለከት አይደለም፡፡[54]

## 4. *መደምደሚያ*

ይህ ፅሁፍ በአጭሩ ለማሳየት እንደሞከረው የአንድ ሰው የቀደመ የወንጀል ታሪክ በድጋሚ ለሚፈፅመው ወንጀል ከሚጣልበት ቅጣት አንፃር በተለያየ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ እንደ ሀገሩ ምርጫ የቀደመ የወንጀል የጥፋተኛነት ሪከርድ ለድጋሚ ወንጀል ቅጣት ሲጣል ጥፋተኛው ማቅለያ እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል ወይም ቅጣቱን ሊያከብድ ይችላል ወይም ውጤት አልባ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የቀደመ የወንጀል ታሪክ ወይም ሪከርድ እንደ ቅጣት ማከበጃ የመጠቀሙ ሁኔታ በስፋት ተቀባይነት ያለው መሆኑን ፅሁፉ አሳይቷል፡፡ በሀገራችንም ያለው አቋም የቀደመ የወንጀል ረከርድ ማቅለያ የማሳጣት እና ቅጣት የማከበድ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የቀደመ የወንጀል ታሪክ እንደ ሁኔታው ልዩ የቅጣት ማከበጃ ሊሆን ይችላል፣ ጠቅላላ የቅጣት ማከበጃ ሊሆን ይችላል፣ ቅጣት ማቅለያ ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ወንጀለኛ የነበረ ሰው በህጉ የተቀመጡ መስፈርቶች አሟልቶ በመገኘቱ ምክንያት ከተሰየመ ይህ የመሰየም ውሳኔ ከተሰጠ ከአምስት ዓመት በኋላ ለሚፈፅመው ወንጀል የቀድሞ የወንጀል ታሪኩ እንደ ቅጣት ማከበጃ ዉጤት አያስገኝበትም፤ እንዲሁም ወንጀለኛው ለቀድሞ ወንጀሉ ምህረት ተሰጥቶት ከነበረ የቀድሞ የወንጀል ሪከርዱ ስለሚሰረዝለት ለቅጣት ማከበጃ አያገለግልበትም፡፡ በሌላ በኩል ይህ ፅሁፍ ለማሳየት እንደሞከረው በሀገራችን የቀደሞ የወንጀል ታሪክ እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማከበጃ ሊያገለግል የሚገባው አንድ ሰው ቀድሞ የተጣለበትን ቅጣት ጨርሶ ከወጣ በኋላ ከቅጣቱ ሳይማር ቀርቶ ሌላ ወንጀል

[53] ከሳሽ የፌደራል ጠ/ዐ/ህግ እና ተከሳሽ አቶ ደጀኔ ፍቃዱ በቀለ፣ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት፣ የመ/ቁ 187647፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የነበረውን የቅጣት አስተያየት እና የፍ/ቤቱን አቋም ከመዝገቡ ማግኘት ይቻላሉ፡፡

[54] አስገራሚው ነገር ተከሳሹ አቶ ደጀኔ ፍቃዱ በቀለ በኋላ ላይ ጥፋተኛ የተባለበት ቼክ ተሰጥቶ የነበረ ቀድሞ ነበር፡፡ ስለዚህ በአንድ ፍ/ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ቀድሞ መሰጠቱ ለውሳኔው መነሻ የሆነው ድርጊት እራሱ ቀድሞ የተፈፀመ ነው ሊያስብል እንደማይችል ከዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

የፈፀመ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የቀደመ የጥፋተኛነት ሪከርድ ስላለ ብቻ በዐ/ሕግ በኩል ሪካርዱን እንደ ቅጣት ማክበጃ ማቅረብ እና በፍ/ቤት በኩል ይህን ሁኔታ ተቀብሎ ቅጣት ማክበድ ተገቢ አይሆንም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በሕግ ባለሙያዎችም ዘንድ መስተካከል የሚገባው አቋም መኖሩን ፅሁፉ አሳይቷል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ የቅጣት ማክበጃን ከወንጀል ሕጉ መንፈስ ውጪ መጠቀም የህጋዊነት መርህን የሚፃረር አካሄድ ነው፡፡